# የመስቀል መዝሙራት

**1.ልዑል**

ልዑል እግዚአብሔር/2/ምስጋና የገባሃል
ለመስቀል በዓል/2/ በሰላም በጤና አደረስከን

**2.ዮምሰ**

ዮምሰ ለዕልያየ (2)
አበርሀ በመስቀልየ
አበርሀ በመስቀል

**3.ወሪዶ እመስቀሉ**

ወሪዶ እመስቀሉ/2/
እመስቀሉ አብርሃ ለኩሉ
እመስቀሉ ለኩሉ አብርሀ

## 4. ጥልን በመስቀሉ ገደለ

ጥልን በመስቀሉ ገደለ (2)
በመስቀሉ ለሰው ልጅ ሰላምን አደለ

**አ.ዝ ..........**

የመስቀሉን ነገርለኛለምንድ ነው
የዳንበት ምስጢርህይወት ክብራችነው
ለሚጠፉት ሁሉ ሀይሉን ለካዱት
ሞኝነት ሆናቸው እንዳያምኑበት

**አ.ዝ............**

አርማችን መስቀል ነው ከፍ ከፍያልንበት
ክርስቶስ ኢየሱስ የተሰቀለበት
አናፍርም በወንጌል ከዳኑት ወገነን
ከሳሻችን ወድቋል ጥንተ ጠላታችን

**አ.ዝ .............**

የደሙ ነጠብጣብ ክብሩ ያረፈበት
የእባቡን እራስ  የቀጠቀጥንበት
አምነን የዳንበት አይተን ያረፍንበት
ክብር ጌታችን ነው መስቀሉ ምልክት

**አ.ዝ ...........**

ሀይሉንአልብሶናልትከሻችን ከብዷል
የመስቀሉን ልጆች ሁሉም ይፈሩናል
ሰላም ስለወጣ ፍቅርና ይቅርታ
አለም ይማረካል ጠዋትና ማታ

## 5.ሀበ ቀራኒዮ

ሀበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት
ሀበቀረ(2) ደብረ መድኃኒት

**አዝ..........**

የመስቀል ቃል ለኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው
ለማያምኑት ሞኝነት ነው
ለእኛ ግን ሕይወት ነው

**አ.ዝ..........**

እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
አንካደው እንመነው ፈጣሪያችን ቸር ነው

**አ.ዝ ..............**

እንመሰክራለን ድንግል( ማርያም) አማላጅናት(2)
አንካዳት እንመናት የአማኑኤል እናት ናት

**አዝ...............**

እኔስ እሄዳለው ግሼን ማርያም
እንደ እሌኒ መስቀል ልሳለም

**አ.ዝ..............**

ሀበ ጥበባት ሀበ ልሳናት
ዮሐንስ(2) ወንጌለ ስብከት

**6. ይትቀደሰ ስምከ**

ይትቀደሰ ስምከ በኃይለ መስቀልከ
በእጸ መስቀልከ ክቡር ዘዓዕበይኮ ለስምከ
ስብሐት ለከ ለባሕቲትከ ልዑል /2/

## 7. du’aa kessa nuu

***Du’aa kessa nuu baste jalaala ketiin nu wamtee wamtee eyyen***
***Galaanni sif hata’u /2/  yaa waaqayyoo***

**8. ዮም በዓለ መስቀሉ**

ዮም በዓለ መስቀሉ በሰማያት በላዕሉ/2/
ወዘነግሠ በምድር /2/ ለአሕዛብ/2/

## 9. jalalan  hundagotee

***jalalaan hundaa hundaa gotee***
***namaa fayyisuf fannoo irra oltee***
***bayyatee jalalii kee (2)***
***yaa waaq galataa kee***

**10. እንተ ተሐንጸት**

እንተ ተሐንጸት  በስሙ ወተቀደሳት በደሙ
ቤተክርስቲያን(2)
ወተአትበት (2) በእጸ መስቀሉ እስመ ኃይል
እግዚአብሔር ላዕሌሃ/2/

**11. ርዕዩ ዕበዩ**

ርዕዩ ዕበዩ ለዕፀ መስቀል (2)
ዘመጠነዝ(2)ትርሲተ ክብርትሀትና ወፍቅር(2)

**12. በመስቀልከ**

በመስቀልከ ርድዓነ/2/
ወበኃይልከ ተማህጸነ(2)

## *13. ኢየሱስ ነው*

ኢየሱስ ነው ድል አድራጊው
በመስቀሉ ያሸነፈው
የሞትን ሃይል ያደቀቀው(2)

**አ.ዝ.........**

ለሚጠፉት ሞኝነት ነው
ለሚድኑት ሃይላቸው ነው
መስቀል መድኃኒት ነው(2)

**አ.ዝ...........**

ለሀዘንተኞች መጽናኛ ነው
ለህሙማን ፈውሳቸው ነው
መስቀል መድኃኒት ነው(2)

**አ.ዝ......**

ለክርስቲያኖች አርማቸው ነው
የድህነት ምልክት ነው
መስቀል መድኃኒት ነው(2)

**አ.ዝ............**

ቆስጠንጢኖስ ድል ያረገው
ጠላቶቹን ያሳፈረው
መስቀልን አንግቦ ነው(2)

## 14. ኃይላችን ነው

ኃይላችን ነው መመኪያችን
ቤዛችን ነው መጽናኛችን
መስቀል ነው መድኃኒታችን/2/

**አዝ...................**

ልጆቹን ከጥፋት ያዳነበት
ወደሕይወት የመራበት
የጠላትን ቀነበር የሰበረበት
ኢየሱስ ድል የነሳበት/2/

**አዝ...............**

የሞትን ቅስም የሰበረበት
ዲያቢሎስን ያሳፈረበት
የሲኦልን ኃይል የረታበት
ኢየሱስ ድል የነሳበት/2/

**አዝ...........**

የሰይጣንን አፍ የዘጋበት
ትዕቢቱን የሻረበት
ነፃነት ይጀበት
አቺየሱስ ድል የነሳበት/2/

***15. መስቀልከ***

መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ
ይኩነነ ቤዛ(4)መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ

## 16 .  Iyyerusaalem Galuuf

Jaalalli Waaqayyoo guyyaa jimaataa fannoorratti mul’ateera /2/
Iyyerusaalem nugalchuudhaaf biyya haaraa/4/
Iyyerusaalem galuuf jajjabaadha yeroo hundaa yaanamoota/2/
Dhiyaateera dhufaatiin Gooftaa dha/4/
Eenyu kan qophaa’e Iyyerusaalem ishee haaraa galuudhaafi/2/
Qulqulloota wajjiin mirga isaa dhaabbachuufi/2/

***17. መስቀል ሃይልነ***

*መስቀል ሃይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ/2/*
ኸኸ *መድሃኒትነ ለእለ አመነ* (2)
*መስቀልኃይልነው መስቀል ብርታት ነው መስቀልቤዛነው* ኸኸ
*መኸኒትም ነው ለእኛ ለምናምነው*

**18. ሰላም ለኢትዮጵያ**

ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ለሃገራችን/2/
ይላክልን /3//ቸሩ አምላካችን

## 19. Galateefamadha

*Galaatefamadha hammaa bara baraatii (2)*
*hamma bara baraati motiidha atii(2)*

**cseee…………**

*Hundaa duraa kan jirtuu*
*lafaaf samiin haa dubbatuu*
*Hundii darbees ni jirataa*
*Yaa waaqaa koo sif galataa*
*Baraan hin danga’uu ulffinni angoon kee*
*Iliil jedheen sii farsaa dhabadhee fulaa kee*

**cseee…………**

*Warri kale mootii turaan*
*Darbaniiru hardhaa hin jiraan*
*Barsoonii fi oggesonii liqifamanii dhumaanii*
*Dhalonii dhalootan barii yoo darbuu baraan*
*Atii ni jirataa mootiin bara baraa*

**cseee…………**

*Ergamonii samii irratii*
*Ni farfatuu maqaa ketii*
*Ilmii namaa jilbifanaa*
*Sii waqeesu suf bitamuu*
*Duressaa iyyomsitee bela’aa qubsitee*
*Adunyaa kanaa irra enyuu sin qixataa*

## 20. ዲያቢሎስ ተመታ

ዲያሎስ ተመታ በመስቀል (4)
የአዳም ልጆች ሁሉ እንበል እልል(2

አ.ዝ........

የነፃነት አርማ የመዳን ጉልበት
መርዙን ከነአውሬው የነቀለበት
ሞትና መርገምን በድል አስወግዶ
የነፃነት ችቦ በመስቀል ነደደ

**አ.ዝ .........**

መስቀል ውበታችን አዲሱ ተፈጥሮ
ይኖራል ዘላለም በልባችን ከብሮ
ድፍረታችን ሆናል ሌላ ትምክህት የለም
የጌታን መከራ ወደነን አንተውም

**አ.ዝ............**

አህዛበ  እመኑ መዳን በመስቀል ነው
በሂወት ይኖራል የእግዚአብሔር ልጅ ያለው
የመስቀሉን ፍቅር የተሸከማችሁ
እልፍ እልፍ በሉ ወደ እረፍታችሁ

**21. ጸጋ ነሳዕነ**

ጸጋ ነሳዕነ ወህይወትነ ረከብነ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ
በኃይለ መስቀሉ/2/
ኪያከ እግዚእ ነዓኩት ወንሴብሃከ እግዚአበሔር/2/

**22. ኃይልነ ወፀንነ**

ኃይልነ ወፀንነ ሞገስነ/2/
ዝንቱ ውዕቱ መስቀል/2/

***23. ወሐቤ ሰላም***

መስቀል ብርሃን ለኩሉ አለም
መሰረተ ቤተክርስቲያን/2/
ወሀቤ ሰላም መድሀኒአለም መስቀል መድህነ ለእለ ነአምን
**ትርጉም**.ምስቀል ብርሃን ነው ለመላው አለም መሰረት ነሰው
ለቤተከርሰቲያን/2/
ሳላምን ሰጪ ነው መድኃኒያለም መሰቀል አዳን ነው ለምናምን ሰዎች

**24. በወንጌሉ ያመናቹ**

በወንጌሉ ያመናችው
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችው

**25.መስቀል አብርሃ**

መስቀል አብርሃ በክዋክብት አሠርገዋ ለኢትዮጵያ/2/
እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ እግዚአብሔር/2/

**26. ይቤሎሙ ኢየሱስ**

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ እመኑ ብየ
ወእመኑ በአቡየ አበርህ /2/ በመስቀልየ

## 27. ዱበርቶታ ኬሳ

ዱበርቶታ ኬሳ ፊለተምቴ ኬና ዋቀዮ ከን አርገቴ /2/
ገመዲ የሮ ሁንዱማ/2/ ያ ማርያሚ ያ ጊፍቲ ኮ አብዲ ኬኛ ኢሱማ

## 28. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን አልል በሉ/2/
አልቀረምተቀብሮ <u>ተገኘ መስቀሉ/2/</u>
በብርሃን ሞላት አለምን በሙሉ
**አዝ…………**
ምን ቢተባበሩ <u>ምቀኞች ቢጥሩ/2/</u>
ቅዱስመስቀሉንምሸሸገው <u>ቢሰውሩ2</u>
አልቻሉምሊያጠፉ ምን ቢተባበሩ/2
አዝ…………
በተራራ ተሰውሮ <u>ለዘመናት/2/</u>
ተጥሎ በተንኮልተደብቆ <u>ከኖረበት/2</u>
ተገለጸ እንሆ በደመራ እሳት(2)
**አ.ዝ……………**
እሌኒ ናት ይህን ሚስጢር <u>ያስገኘችው(2)</u>
ደመራን በቦታውበክብር <u>ያስቆመችው(2)</u>
የተንኮልንተራራ ያስቆፈረችው(2)
**አ.ዝ…………..**
ታሪካዊ የክርስቶስ <u>ህያው መስቀል(2)</u>
ይኸው ተገለጠ በክብር <u>በግሩም ሀይል(2)</u>
ምን ግዜም ሲያበራ እንዲህ ይኖራል(2)

**29 . ኢትዮጵያ ታበፅዕ**

ኢትዮጵያ ታበፅዕ ኢደዊሃ(2)ሀበ እግዚአብሔር
እንዘትብል አምላኪየ (2)ነፅረኒ ወአድነኒ እም ኃይለ ፀላይወፀር (2)

***30. ዕሌኒ ንግስት***

ዕሌኒ ንገስት ሐሰሰት መስቀሉ (2)
ዕንባቆም ኑበይ ዘአንከረ ግብሮ(2)

**31. ኀበሩ ቃል**

ኀበሩ ቃል ነቢያት/2/
ወይቤሎ መስቀል ብርሃነ/2/ ለኩሉ አለም/2/

**32. መድኃኒት**

መድኃኒት እፀ-ህይወት (2)
ዝንቱ ውዕቱ መስቀል(4)

## 33. እፀ መስቀል

እፀ መስቀል የክብር መውረሻ
ሰይጣንን ድል መነሻ
**አዝ………**
የክብር ባለቤት እፀ መስቀል
የተሰዋበት ››
እፀ መሰቀሉ ነው ››
የአለም መድኃኒት ››
**አዝ…….**
እነደ እሌኒ ንግስት እፀ መስቀል
ፍጹም አክብራችሁ ››
ሁላችሁ ገስግሱ ››
መስቀሉን የዛችሁ ››
**አዝ……**
ያለ ኃይለ መስቀል እፀ መስቀል
የሰላም አርማችን ››
ሊሸነፍ አይችልም ››
ሰይጣን ጠላታችን ››
**አዝ……….**
እሳተ መለት እፀ መስቀል
ያላቃጠለው ››
ሰይጣንን የሚያግድ ››
እፀ መሰቀል ነው ››
**አዝ…………**
እነደተባረከው እፀ መስቀል
ቆሰጠነጢኖስ ነጉስ ››
በመስቀል ብርሃን ››
ወደ እውነት እንገስግስ ››
**አዝ……**
የተዋሕዶ ልጆች እፀ መስቀል
ገስግሱ በተስፋ ››
እፀመስቀል ያዙ ››
ጠላት እንዲጠፋ ››

## 34.በመስቀል እንመካለን

በመስቀል እንመካለን እንድበታለን
መስቀልመታመኛችን ለኛመመኪያችን
**አ.ዝ……………..**
በክርስቲያኖችዘንድመስቀልሃይላችን
የመስቀል ምልክት ›› ››/2/
ሐይልና ጋሻነው ›› ››
በእምነት ለያዙት ›› ››
**አ.ዝ……………**
አምላክየእኛንበደልመስቀልሐይላችን
የተሸከመበት ›› ››/2/
የከበረ ደሙ ›› ››
ነው የፈሰሰው ›› ››
**አ.ዝ………………**
የመለኮት ስጋ መስቀል ሀይላችን
የተፈተተበት ›› ››/2/
መስቀል ሃይላችን ነው ›› ››
የምንድንበት ›› ››
**አ.ዝ…………….**
ነጻ የወጣበት መስቀል ሃይላችን
አዳም ከመከራ ›› ››/2/
የቀራኒዮ ሰንደቅ
ለኛሀይላችን
**አዝ………….**
አንባ መጠጊያችን መስቀልሃይላችን
ድንቅ ማሕተባችን
ልብ ያለው ልብይበል
ይሳል በልባችን
**አዝ………**
ለኛ መመኪያችን መስቀል ሃይላች
ጠላትን ድል መንሻ
የቅዱሳን ምርኩዝ
መስቀል የእኛ ጋሻ

## 35. Lola fanno

Lola fannosaatiin ajeese (2)
Fanosaatiin namootaaf fayyumma nu hire(4)

## 36. በመስቀሉ

በመስቀሉ ወበቃሉ/2/
አዕዮሙ ለአበዊነ አዕበዮሙ ለአበ ኸኸ

## 37. መስቀል ተመርኩዘን

መስቀል ተመርኩዘን ወንጌል ተጫምተን
ሃይማኖትን ሰብከን በክርስቶስ አምነን
ማን ያሸንፈና እኛ ክርስቲያንን
ክርስቶስ አለልን
**አ.ዝ…….**
ንግስቲቷ እሌኒ በጣም የታደለች በጣን ጢስ ተመርታ መስቀሉን
አገኘች መዳኒት ስትፈልግ ኪራኮስን ይዛ
መስቀሉን አገኘች የአለሙን ቤዛ
**አ.ዝ………..**
ከሙታን ተነስተው ያመሰገኑት
ዕፀ መስቀሉ ነው የእኛ መዳኒት
መስቀል ምርኩዛችን ጎዳናው ወንጌል
ወደ ገነት እንጂ አንሄድም ሲኦል
**አ.ዝ……..**
ንዑ ንወድሳት ለዕፀ መስቀል
የተሸከመውን የአምላክን ቃል
ንዑ ንወድሳት ለማርያም ድንግል
አክሊለ ምዕመናን መርሃ ዘወንጌል

## *38. እዩት የመስቀሉን ብርሃን*

እዩት የመስቀሉን ብርሃን (3)
ፍጥረቱን ሲያድን
**አ.ዝ…….**
ስንቱ ይነገራል የእግዚአብሔር ቸርነት
ለሰቀሉት አይሁድ የለመነ ድህነት
ማስተዋል ላደለው ለቻለ መመልከት
ይህ ነው አይባልም የእግዚአብሔር በረከት
**አ.ዝ………**
መስቀል አበባ ነው ትግስትን ላደለው
ሂውትን ለማዳን የሚያገለግል ነው
ለመስቀል በረከት ልዩ ነው ፍቅራችን
ስጋውና ደሙ የሂውት ምግባችን
**አ.ዝ…….**
ቅድስቲቷ እሌኒ አምላክ የመረጠሽ
መስቀሉን አገኘሽ በፍቅሩ ተቃጥለሽ
የመስቀሉ መዓዛ ልብሽን አውዶሽ(2)
**አ.ዝ………….**
እልል እልል እንበል እንዘምር በደስታ
ድንቅ አድርጎልናል የሰራዊት ጌታ
መስቀል ከበራበት ጭለማው ልባችን
እኛም ልጆቹ ነን እሱም አባታችን

## 39. ብርሃን ወጣ

ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንጸባርቅ
የምላክና የሰው ልጆች እውነተኛ እቅ
ደስይበለን በመስቀሉ ብርሃን
እልል እንበል በአንድነት ሆነን
ተገኘልን መስቀል ሃይላችን
**አ.ዝ…………**
ከፊትለፊት በመሳሉየመስቀሉ ነገር
የሚወደውሐዋርያ የወንጌል መምህር
ዮሐንስም ስቅለቱን በማየቱ
ሲያዝን ኖረ በምድራዊ ሕይወቱ
ቢያሰቅቀው ሞቱ ግርፋቱ
**አ.ዝ……….**
ሞኝነት ነው ለሚጠፉትመሰናከያቸው
ባለም ጥበብለሚኖሩት እውነት ተስናቸው
ለጠቢብ ሰው በመንፈስ ለሚኖሩት
የመዳን ቀን እውነተኛ አርማነው
ከገሃነም እሳት ሚያድን ነው
**አ.ዝ…………**
እሰከሞቱ ያልተለየው ቅዱስ ሐዋርያ
ለዮሓንስ የወንጌል ሰው የፍቅር ባለሙያ
ምስጋናችን ከምድር ይድረሰው
እንድናለን በሰጠው ምሳሌው
ሰዎች ሁሉ እንከተለው

## 40..መስቀል አበባ

መስቀል አበባ ነው ውብ አበባ
አደይ አበባ ነሽውብ አበባ
**አዝ………**
መስቀል አበባ ጥራጊውን ሞልተው
›› ›› አይሁድ በክፋት

›› ጢሱ ሰገደ
መስቀለ ካለበት
ተሰውሮ ሲኖር
ስነ ሰቅለቱ
እሌኒ አገኘች
ደገኛይቱ

**አዝ……….**

መስቀል አበባ ግማደ መስቀሉ
የጌታችን
ምስለ ፍቁር ወልዳ
እመቤታችን
የሚካኤል ጽላት
ይዘው ታቦቱን
ምስከረም መባቻ
በአስረኛው ቀን
ከግበጽ ወጡ
በዳዊት ዘመን

**አዝ………..**

መስቀል አበባ ከመስቀሉ ስር
ታምሩን ሰራ
ደዌ ፈወሰ
እውራን አበራ
ለምጻሙም ነጻ
ጎባጣውም ቀና
አጋንንት ወጡ
ከሰው ልቦና
ፍቅር አንድነት
ሆኖልናልና

**አዝ…….**

መስቀል አበባ መስቀሉን ወስደው
ከመስቀልያ ስፍራ
በግሼን አኖሩት
በአንባሰል ተራራ
የመስቀሉ ዜና
ደስታን አበሰሩ
አሸብርቀው ደምቀው
ለእርሱ መሰከሩ

## 41. ኢይኃድጋ

እይኃድጋ /3/ ኧኸ ለሃገሪትነ ኢትዮጵያ/2/
አይተዋትም/3/ ሃገራችንን ኢትዮጵያን/2/

## 42. መስቀል ኃይልነ

መስቀል ኃይልነ መስቀል ፅንነ
መስቀል ቤዛነ መድኃኒትነ
መስቀል ኃይልነ

**አ.ዝ………………**

ለተቀበልነው ለምናምነው
መስቀል ሃይላችን አርማችን ነው
ዲያቢሎስ መምቻ የሰላም ጥላ
መስቀሉን ይዘን አናይም ኋላ

**አ.ዝ………………**

ከቀራንዮ ጎለጎታ
የተሰጠን ታላቅ ስጦታ
ሰላሙ አለ መስቀሉ ላይ
እዩት ሲያበራ እንደ ፀሐይ

**አ.ዝ………………**

መድኃኒዓለምን የወደደው
መስቀሉን ይሸከም ይከተለው
እራሱን ይካድ ነፍሱንም ይስጥ
በአህዛብ ምክር ሳይናወጥ

**አ.ዝ………………**

ያላመናችሁ ኑና እመኑ
በመስቀሉ ቃል እንድትድኑ
የምስራቹን ሰላም ይሰብካል
ጠላትን አስሮ ያንበረክካል

## 43.እሰይ እልል በሉ

እሰይ እልል በሉ ተገኘ መስቀሉ(4)

**አ.ዝ…………**

የጥል ግድግዳ አበባ
የፈረሰበት ››
ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ››
የታረቀበት ››
የእግዚአብሔር ልጅ ››
የነገሰበት ››
የሞት አበጋዝ ››
የወደቀበት ››

**አ.ዝ……………**

አይሁድ በቅናት አበባ
መስቀሉን ወስደዉ ››
ቢቀብሩት እንኳን ››
በቆሻሻቸው ››
ጌታን መቃወም ››
ስለ ማይችሉ ››
የይኸው ተገኘ ››
ወጣ መስቀሉ ››

**አዝ……………**

ደጉ ኪራኮስ አበባ
ሽማግሌው ››
እሌኒን መራት ››
በደመራው ››
ጌታ በሱ ላይ ››
በመሰቀሉ ››
ጢሱ ሰገደ ››
ወደ መስቀሉ ››

**አዝ…………….**

የእምነት ምልክት አበባ
መስቀል ነውና ››
ተራራው ሜዳ ››
ሆነ እንደገና ››
እንደ ተነሳ ››
ጌታ በቃሉ ››
ከጉድጋድ ወጣ ››
ዕፀ መስቀሉ ››

**አ.ዝ……………..**

እኛም በስቀል አበባ
እንመካለን ››
በእግዚአብሔር ጥበብ ››
መቼ እናፍራለን ››
ሞኝነት እንኳን ››
ቢሆን ለዓለም ››
ኃይልህ እውን ነው ››
ለዘላለም ››

**አ.ዝ………………**

ግድግዳው ፈርሷል አበባ
የልዩነቱ ››
ምድርና ሰማይ ››
ሆኑ እንደ ጥንቱ ››
ነብስና ስጋ ››
በእርሱ ታርቀዋል ››
ህዝብና አህዛብ ››
ወንድም ሆነዋል ››

## 44.በኃይለ መስቀሉ

በኃይለ መስቀሉ/2/ ይቀበነ/2/
በኃይለ መስቀሉ/3/ ይቀበነ/2

## 45. እሰይ አበራ

እሰይ አበራ መስቀሉ ለአለም ሁሉ
ይለኮስ ችቦ ደመራው ጨለማው ይብራ

**አ.ዝ…………**

የጥል ግድግዳ ፈረሰ እሰይ አበራ
ዳግም እንባችን ታበሰ ›› ››
ሕይወት ነው ለኛ መስቀሉ›› ››
ታምነናልና በቃሉ ›› ››

**አ.ዝ………………**

አይሁድ በክፋት ቢነሱ ›› ››
የሀሰት ካባ ቢለብሱ ›› ››
እሌኒ ሄደች ገስግሳ ›› ››
ቆስጠንጢኖስን አንግሳ ›› ››

**አ.ዝ…………………**

ዛሬምሀይል አለው መስ እሰይአበራ
አንድ አልፎበታል ለሁሉ ›› ››
አንሸሽገውም ከእውነት ›› ››
መውጊያውን ስለወጋበት ›› ››

**አ.ዝ………..**

የመስቀሉቃል ላመነው እሰይአበራ
ከሞት ማምለጫ ስንቅ ነው ››››
ለአለም ቢመስልም ሞኝነት ›››
ተከፍሎበታል ስርየት

## 46.ምንአይነት

ምን አይነት ሚስጥር ነው
ምን አይነት ጥበብ ነው
ኣምላክ በመስቀሉ ለኛ የገለጠው(2)

**አ.ዝ…………**

የሰላም ምልክት የፍቅርመሰረት (2
የክርስቶስ መስቀል ያስደንቃል በእውነት(2)

**አ.ዝ………..**

የነጻነት ፋና የህይወት ወጋገን (2)
በእውነት የሚገለጥ ዘላለም ብሃን(2)

**አ.ዝ…………..**

የህያዋን ምርኩዝ የደህነት አርማ(2)
የህይወት መሰረትየአንድነትአላማ2)

**አ.ዝ………………**

የዲያቢሎስ መምቻ ጠላትማሳፈሪያ(2)
እውነተኛ አለኝታ የሰዎች መመኪያ(2)

**አ.ዝ……….**

እናት የተሰጠን እንድንመካባት(2)
ከመስቀሉ ስር ነው እነሆ ያገኘናት(2)

## 47.የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር ሲገባን/4/
እመቤታችንን እናያታለን
የመሰቀሉ ፍቅር የገባቸው/4/
እመቤታችን አለች ከጎናቸው

**አዝ……………**

አባ ሕርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ፍቅር ሲገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤታችን ጋር ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር

**አዝ………..**

ለመናኒው ጸሎት ልዩ እጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እሙብርሃን
መዓዛው ሸተተን ከግሼን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኝማለሽ ምን ልሁን

**አዝ…………..**

ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድነኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሃገር የሚሉሽ
እመቤቴ ማርያም አነቺው ነሽ/2/

**አዝ…………**

ቤተልሔም ስሔድ አይሻለው
ቀራንዮም ስሔድ አይሻው
ፍጹም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ/2/

## 48.አይሁድ በተንኮል

አይሁድ በተንኮል ምንም ቢሰውሩት
አልቀረም ተቀብሮ ተገኘ መስቀሉ
ሀሌ (3) ሉያ እንበል /በሉ

**ኢ.ዝ..........**
ኢየሱስ በደሙ የቀደሰው መስቀል
አልቀረምተቀብሮ ወጣ በታላቅ ድል
ሀሌ (3)ሉያ እንበል
**ኢ.ዝ.............**
ግሩም ድንቅ መስቀል እፀ መድሃኒት
ተገለጠ ዛሬ በደመራ እሳት
ሀሌ (3)ሉያ እንበል
**ኢ.ዝ...........**
የመስቀሉን ሚስጢር የገለፅላት
ደመራ ኣስተከለች እሌኒ ንግስት
ሀሌ (3) ሉያ እንበል

***49.ዘእጣን አንጻረ***

ዘእጣን አንጻረ/2/ /4/
በኅለኅታ ተረክበ እጸ መስቀል
እጣኑም አሳየ/2/በኅለኅታ ተገኘ እጸተመስቀል

**50.ኾኸ በመሸቀልከ**

ኽበመስቀልከ ኸኽ ጽልመተ አብራዕከ
›› ›› ›› ሙታን አንሳዕከ
ኾኸወዘተሃጉለ ረዳይከ በመስቀልከ/2/

**51. እንተ ተሐንጸት**

እንተ ተሐንጸት በስሙ ወተቀደሳት በደሙ
ቤተክርስቲያን(2)
ወተአትበት (2) በእጸ መስቀሉ እስመ ኃይል
እግዚአብሔር ላዕሌሃ/2/

## 52. ከመ ትባርከነ

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ/2/
ኸኸ ተዋነይ በጽድቅ/4/ እስጢፋኖስ
ሐመልማለ ወርቅ /2/ ኸኸ/3/

***53. ዝንቱ መስቀል***

ዝንቱ መስቀል ቤዛነመድሃኒትነ /2/
ዝንቱ መስቀል ቤዛነ መድኀኒት/1/ነ/2/ት)
ይሔ መስቀል ቤዛ ነው መድሃኒትም ነው(2)

## 54.አንቲ ዘበአማን

አንቲ ዘበአማን (2)
ርኅብኪ ፀጋይ ክብር ድንግል
ያቢ ገብራን ለማርያም
**አዝ...........**
በግሸን ተራራ ዘበአማን
በክብር ተቀምጠሻል "
ታላቁን በረከት "
በጅሽ ጨብጠሻል "
እንሰግድልሻለን "
የፀጋ ስግደት "
እመቤቴ ማርያም "
የጌታዬ እናት "
**አዝ...........**
ልሂድ ወደ አንባሰል ዘበአማን
ወደ ግሸን አንባ "
አድርጊኝ እንደ ህፃን "
ወደ ቤትሽ ልግባ "
ልረፍ በመስቀሉ "
ከደጅሽ መጥቼ "
የአለምን ጫጫታ "
ሁሉን እረስቼ "
**አዝ..........**
አሩቅ ነዉ መንገዱ ዘበአማን
ብርቱ ነዉ ዳገቱ "
ንገሪዉ ለልጅሽ "
የርሱ ነዉ ጉልበቱ "
ሳረግፍ እንደ አበባ "
ሳልመጣ በአልጋዬ "
ህይወቴን አደራ "
ነብስና ስጋዬን "
**አዝ.............**
ያመሰግኑሻል ዘበአማን
አለም ዘለአለም "
ስምሽ ይጣፍጣል "
ድንግል ማርያም "
በተሰጠሽ ፀጋ "
በአንቺ አማላጅነት "
ለልጆችሽ ይብዛ "
እድሜና በረከት "

## 55.በወንጌል

በወንጌል በወንጌል
እናመናለን እኛ በወንጌል
**አዝ........**
በሰላም ምልክት በወንጌል
በክብር መገኛ
በቅዱስ ወንጌሉ
እናምናለን እኛ
**አዝ.............**
ሰይጣን ድል ተመታ በወንጌል
ሰላም ተበሰረ
ፅድቅ የተራቆተ
ፀጋን ተቀበለ
**አዝ..........**
ያዘነው ይፅናናል በወንጌል
በርቱን ተደግፎ
እንባው ይታበሳል
ደስታን ትንናፅፎ
**አዝ............**
አለም ብርሃን አየ በወንጌል
ጨለማ ተረታ
ወንጌል ሲተረጎም
ምስጢሩ ሲፈታ
**አዝ................**
ሰላምን አገኘ በወንጌል
ልባችን በደስታ
መናፍቅ አፈረ
በወንጌል ተረታ
**አዝ........**
የክህደትን መፃፍ በወንጌል
ቢያበዙ ቢያሰፉ
ወንጌል ብርሃን ነው
የተማር ነው ከእሱ
**አዝ..........**
አበው ሊቃውንቱ በወንጌል
እንደተናገሩት
እምኑ ብለዋል
በቅዱስ ወንጌል
**አዝ.........**
በሕዝቅኤል ትንቢት በወንጌል
እንደተነገረ
ይህን መፅሃፍ ብላ
ተብሎ እንደተፃፈ
በወንጌል በወንጌል
ነኣምን በአሃዱ በወንጌል

## 56. አለው አለው

አለው አለው ሞገስ
የመስቀል በዓል ሲደርስ
አለው አለው አበባ
የመስቀል በዓል ሲገባ
አለው አለው ደስታ
መሰቀል ሲከበር በአልልታ
አለው አለው ሰላም
መስቀል ሲታይ በአለም
አለው አለው አለኝታ
ዕፀ መስቀል መከታ
እዩት እዩት ሲያበራ
የመስቀልበዓል ደመራ
እዩት እዩት ሲያምር
መሰቀል በአለም ሲከብር

## 57.የኛ ነው ዋሻው እምነቱ

የኛ ነው ዋሻው እምነቱ ፀበሉ
አናፍርም ትምክህታችን ነው መስቀሉ/2/
የኛ ነው የኛ የኛ/2/

የሶስት ሺህ አመት የኛ
ታሪክ ያላት የኛ
ታቦተ ፅዮን የኛ
ያለችበት የኛ
የፀሎት ስፍራ የኛ
የኪዳን ሀገር የኛ
ኢትዮጵያ ሀገሬ የኛ
ሀገረ እግዚአብሔር የኛ
**አዝ...........**
ከአንድ ድንጋይ የኛ
የተወቀረው የኛ
የላሊበላ የኛ
ድንቅ ስራ ነው የኛ
ጣራው ክፍት ሆኖ የኛ
ዝናብ ማይገባው የኛ
አቡነ አሮን የኛ
ምንኛ ውብ ነው የኛ
**አዝ...........**
ኢትዮጵያ ሀገሬ የኛ
ልጅሽ ባርኮስ የኛ
ተጠምቆልሻል የኛ
በፊሊጶስ የኛ
የምላክ ሠው መሆን የኛ
ምስጢርን አውቆ የኛ
በኢየሱስ አምኖ የኛ
መጣ ተጠምቆ የኛ
**አዝ...........**
ትምክህታችን ነው የኛ
የጌታ መስቀል የኛ
አምነን ድነናል የኛ
በእምነት በፀበል የኛ
መለያችን ነው የኛ
ማህተባችን የኛ
ተዋህዶ ናት የኛ
እምነታችን የኛ
**አዝ...........**
ፃድቃኔ ሒዱ የኛ
ሸንኮራ ሒዱ የኛ
ግሸንም ውጡ የኛ
አክሱም ውረዱ የኛ
ሽባው ተፈቶ የኛ
እውሩ በርቶ የኛ
ጎባጣው ቀንቶ የኛ
ደንቆሮው ሠምቶ የኛ
ፍፁም አምነናል የኛ
አይናችን አይቶ የኛ
ፀንተን ቆመናል የኛ
ጆሯችን ሰምቶ የኛ

## 58. Naakenni Waaqayyoo

Naakenni Waaqayyoo sammuuf qalbii yeroo hundaa kan siyaadu /2/

Lubbuukoos naataasisi seerakee qofaan kan gammadduu /2/

## 59. ኖላዊነ ሔር መድሐኔዓለም

ኖላዊነ ሔር መድሐኔዓለም
ለነፍስ ወሲሥጋ ወለኩሉ ዓለም
ዕቀበነ ዕቀበነ ዕቀበነ ለዓለም ዓለም/፪/
**አዝ............**
ድምጼን ይለዩታል በጎቼ በሙሉ

አያሥታቸውም መንገደኛ ሁሉ
በራሡ በአምላክ የተባለላችሁ
በጎች ተሠብሰቡ ወደ በረታችሁ

**አዝ............**

ነብይ ነኝ የሚል የሠፈር ዜናዊ
አድርጎ የሾመ ራሡን ወንጌላዊ
ነጣቂ ተኩላው ተበራክቷልና
መንጋኸን ጠብቀው በዕምነት እንዲጸና

**አዝ............**

ከአምላክ የተላከ እውነተኛ እረኛ
ለመንጋው የሚያስብ ያይደለ ምንደኛ
ፊት የተማረ ነው ኋላም የተሾመ
በሐዋርያዊ ክኅነት በእውነት የታተመ

**አዝ............**

ከጌታ የመጣ ከአልሆነ ክኅነቱ
ከአበው የተለየ ከሆነ ትምሕርቱ
በበሩ የአልገባ ሌባ ነው ሥለ አለ
ምዕሡናን አትስሙት አሣቹ ሥለ አለ

**አዝ............**

ጩኸታችን ሠምተኸ ጭንቃችን አይተኸ
በየዘመናችን የሚታደግ ልከኸ
እውነተኛ መምሕር የበጎች እረኛ

አንተው አሠማራን ተመልከት ወደ እኛ።

## 60.ኢትየጵያ ሰላምሽ

ኢትዮጵያ ሰላምሽ ይብዛ
ተጠለይ በእግዚአብሔር ታዛ

**አዝ............**

ከሚራራልን ፍቅር ከሆነው
ዘላቂ ሰላም እግዚአብሔር ነው
ይህን እወቂ ይህን ተረጂ
በልብሽ ጉልበት ለእርሱ ስገጂ

**አዝ...............**

በሰይፍ ያልቃሉ ሰይፍ የሚያነሱ
የሚራራልን ሲፈርድ ንጉሱ
በቀል የእርሱ ነው አይደለም ያንቺ
በጸጋው ታጥረሽ በጸሎት በርቺ

**አዝ..............**

የውጣ ወረድ የጉስቁልናው
በእግዚአብሔር ነው መከራ ማብቂው
ሠላ ይሁን ሲል ይሆናል ሠላም
ያሳየሽውን ሠላም አይረሳም

**አዝ...........**

ማራት ኢትዮጵያን ማራት ሃገሬን
በየሄድኩባት መጥሪያ ስሜን
ይብቃት ለሊቱ ይውጣላት ጸሐይ
አሁን ይዘርጋ እጅህ ከሰማይ

**አዝ...............**

እንድትፈራርስ ጠላት ሸምቋል
ብርቱውን ጉልበት ከአፈር ደባልቋል
ይህን ግፍ አስብ ዘንበል በልላት
ካንተ በስተቀር መሄጃም የላት

## 61.ለዕፀ መስቀሉ

ለዕፀ መሰቀሉ እንስገድ/2/
ጠላት እንዲጠፋ እንዲሆን አመድ
ዕፀ መስቀሉን ያዙ ጋሻ/2/
ሰይጣን እንዲወገድ እንዲያጣ መሸሻ
እፀ መስቀሉን ተሳለሙ/2/
የአምላክ ሃይል አለበት ደመ ማህተሙ
መስቀል ሃይል ነው ለክርስቲያን/2/
እርሱን የያዘ ሰው አይደፍረውም ሰይጣን
ዕፀ መሰቀሉን እንጠጋ/2/
ተበታትኖ እንዲወድቅ የዲያቢሎስ መንጋ
ዕፀ መስቀሉ ያኮራናል /2/
እርሱን ከተጠጋን ጠላት ይፈራናል
መመኪያችን ነው መስቀል /2/
ተቀደሷል እና በመለኮት ሃይል

## 62. መስቀል የኛ መዳኛችን

መስቀል ኃይላችን
መስቀል ቤዛችን
መስቀል የኛ መዳኛችን/2/

**አዝ............**

አይሁድ ቢሸሽጉት መስቀሉን ጠልተው
**መስቀል ዕፀ መስቀል**
እውነትን ሊያጠፉ ከጉድጓድ ቀብረው
**መስቀልእፀ መስቀል**
ነገር ግን አልቻሉም እውነትን ሊያጠፉ
**መስቀል ዕፀ መስቀል**
ምንም ሳይሆን ኖረ መስቀሉ ባለበት/2/

**አዝ.............**

እሌኒ ናት ያገኘችው
**መስቀልዕፀ መስቀል**
ደመራን ደምራ ያስቆፈረችው
**መስቀል ዕፀ መስቀል**
ጭሱ እየመራ ቦታውን አሳየ
**መስቀል ዕፀ መስቀል**
በሚሰራው ታምር ከሌላው ተለየ/2/

**አዝ..........**

ግሼን አነባ ላይ ነው መስቀሉ ያረፈው
**መስቀል ዕፀ መስቀል**
ግማደ መስቀሉ እውነተኛ ነው
**መስቀል ዕፀ መስቀል**
አሁንም ይሰራል ስፍራውንም ባርኮ
**መስቀልዕፀመስቀል**
ማንስ ይጨርሳል ታሪኩንተርኮ/2/

**አዝ........**

እልልታ አለው መስቀል ሲወጣ
መስቀልዕፀመስቀል
አገር እንዲባረክመከራ እነዳይመጣ
መስቀል ዕፀ መስቀል
ከፍ ብሎ ይታያል በተራራው ስፍራ
መስቀል ዕፀ መስቀል
መስቀል ኃይላችን ነው ይኖራል ሲያበራ/2/